# የ MEMORIAL HERMANN HEALTH SYSTEM ፖሊሲ

**<u>የፖሊሲ አርእስት:</u>** የክፍያ አጠያየቅ እና አሰባሰብ ፖሊሲ

**የታተመበት ቀን:** 03/19/2018
**እትም:** 1

---

**<u>የፖሊሲ አላማ:</u>**

ፖሊሲው በ Memorial Hermann Health System (“MHHS”) ወይም ኮንትራት የተሰጣቸው ውጫዊ ሰብሳቢ ኤጀንሲዎች ሊወሰዱ የሚችሉ እርምጃዎችን ጨምሮ ምክንያታዊ የታካሚ ሒሳብ አሰባሰብ አሰራሮችን ዘርግቷል።

**<u>ተግባራዊ የሚሆንባቸው ቦታዎች:</u>**

ፖሊሲው በሁሉም በክፍል 501(c)(3) MHHS ሆስፒታሎች የሚተዳደሩ እና የ MHHS ገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ ሽፋን ያላቸው ከመንግስት ፈቃድ የተሰጣቸው የሆስፒታል ተቋማት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል:

Memorial Hermann Greater Heights Hospital
Memorial Hermann Katy Hospital
Memorial Hermann Memorial City Medical Center
Memorial Hermann - Texas Medical Center
- Memorial Hermann Cypress Hospital
- Memorial Hermann Orthopedic and Spine Hospital

Memorial Hermann Northeast Hospital
Memorial Hermann Rehabilitation Hospital Katy, L.L.C.
Memorial Hermann Southeast Hospital
- Memorial Hermann Pearland Hospital

Memorial Hermann Southwest Hospital
Memorial Hermann Sugar Land Hospital
Memorial Hermann The Woodlands Medical Center
TIRR Memorial Hermann

MHHS የተመላላሽ ታካሚዎች ኢሜጂንግ ማእከላት፣ የስፖርት መድኃኒት እና ማገገሚያ ማእከላት፣ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱት ሆስፒታሎች ስር የሚገኙ የተመላላሽ ታካሚዎች ክፍሎች አቅራቢዎች ላይ የተመሰረቱ የአስቸኳይ ሕክምና ማእከላት የሚያስተዳድር ሲሆን፣ በዚህ ፖሊሲ ሽፋን የሚያገኙ ናቸው።

**<u>የፖሊሲ መግለጫ:</u>**

1. MHHS እና አብረውት በገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ ስር የሚሰሩ ተቋማት ለአገልግሎቶች የመክፈል አቅም ካላቸው ታካሚዎች የታካሚ ሒሳብ የመሰብሰብ ፖሊሲ ይከተላሉ። ይህ ፖሊሲ ለ MHHS ታካሚዎች የቀረቡ የሆስፒታል እና/ወይም ሌሎች አገልግሎቶች ክፍያዎች ለመሰብሰብ MHHS ሊወስዳቸው የሚችል እርምጃዎችን ያብራራል። ፖሊሲው የአሰባሰብ እንቅስቃሴዎቹ ሂደት እና የጊዜ ገደብ፣ ከስራአጥነት ጋር በተያያዘ MHHS የሚወስዳቸው እርምጃዎች፣ እንዲሁም አንድ ታካሚ ለገንዘብ ድጋፍ ብቁ መሆኑ እና አለመሆኑ ለመወሰን MHHS ሊያደርጋቸው የሚገቡ በቂ ጥረቶችም ያብራራል።

*ማስታወሻ: የታተሙ የዚህ ሰነድ ቅጂዎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው አይደሉም። በታተመው እና ኤሌክትሮኒካዊ በሆነው የዚህ ሰነድ ይዘት መካከል አለመጣጣም ሲኖር፣ ቁጥጥር የሚደረግበት የታተመው የፖሊሲ፣ አሰራር፣ እንዲሁም የመመሪያ አስተዳር ስርአት እትም ተቀባይነት ይኖረዋል።*

2. ይህ ፖሊሲ ታካሚዎች በ MHHS ለሚቀርቡላቸው አገልግሎቶች መክፈል ስለሚገባቸው የክፍያ መጠን MHHS እንዴት ሊያናግራቸው እንደሚገባም ይገልጻል።

3. MHHS ለገንዘብ ድጋፍ ብቁ ሊሆኑ የሚችሉ ታካሚዎችን በመለየት ረገድ በቂ ጥረት ያደርጋል።

4. ይህ ፖሊሲ MHHS የታካሚን ሒሳብ የባከነ ወይም የከሰረ እዳ የሚያደርግባቸው እንዲሁም የታካሚ የሒሳብ መጠኖችን እንደ ኪሳራ ወይም እንደማይከፈሉ የመቁጠር አሰራር የመቆጣጠር እና የመከታተል ሂደትን ያባራራል።

5. በውስጥ ገቢዎች ኮድ ክፍል 501(r) እና ይህንን ተከትለው በወጡ ሕገደንቦች በግልጽ እንደተገለጸው፣ MHHS በእጅግ ልዩ የአሰባሰብ ተግባራት አይሳተፍም።

6. እነዚህ ከላይ የተቀመጡት ፖሊሲዎች እና አሰራሮች ለቴክሳስ ግዛት ሕጎች እና ደንቦች፣ ለውስጥ ገቢዎች ኮድ ክፍል 501(r)፣ እና ለተዛማጅ መመሪያዎች ተገዢ ይሆናሉ።

7. MHHS የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ ብቁነት ለማረጋገጥ በቂ ጥረት ማድረጉን የማረጋገጥ ሙሉ ስልጣን ለ MHHS የተሰጠ ነው።

**<u>ቃላቶች እና ፍቺዎቻቸው:</u>**

1. *ማመልከቻ:* በታካሚው የሚሞላ የገንዘብ ድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻ ነው።

2. *የማመልከቻ ጊዜ:* በማመልከቻ ጊዜው፣ MHHS የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ ተቀብሎ ያስኬዳል። የማመልከቻ ጊዜው ሕክምናው ለግለሰቡ በተሰጠበት ቀን ተጀምሮ ከመጀመሪያው የህክምናው የክፍያ መግለጫ ቀን በኋላ በ 240ኛው ቀን የሚጠናቀቅ ይሆናል።

3. *የባከነ ወይም የማይከፈል እዳ እንደ ኪሳራ መቁጠር።* ታካሚው ያልተከፈሉ እዳዎችን የመክፈል አቅም እያለው፣ ሊሰበሰቡ አይችሉም ተብሎ ለታመነባቸው ክፍያዎች የታካሚው ሒሳብ ላይ የሚደረግ ማስተካከያ። ውሳኔው በተቀመጡት መስፈርቶች መሰረት የሚደረግ ሲሆን፣ ሒሳቡ ክፍያ ከተጠየቀ እና በቂ የክፍያው መሰብሰብ ጥረቶች ከተደረጉ በኋላ ብቻ ነው።

4. *የኮንትራት ማስተካከያ:* በታካሚው ጠቅላላ የክፍያ መጠን እና በሕገደንቦች እና በኮንትራት ውሎች መሰረት ከሶስተኛ አካል በሚያገኘው ማካካሻ ክፍያ መካከል ያለው ልዩነት ለማሳየት የታካሚው ሒሳብ ላይ የሚለጠፍ ማስተካከያ ነው።

5. *እጅግ ልዩ የአሰባሰብ እርምጃዎች (“ECAs”):* እነዚህ የሕግ ወይም የፍርድቤት ሂደትን የሚጠይቁ እንዲሁም እንደ እዳ ለሌላ አካል መሸጥ ወይም ተቃራኒ የክረዲት መረጃ ለክረዲት ኤጀንሲዎች ወይም ቢሮዎች ሪፖርት ማድረግ የመሳሰሉ እንቅስቃሴዎችን ሊያካትቱ የሚችሉ የአሰባሰብ እርምጃዎች ናቸው። **MHHS ECAs ላይ እጁን አያስገባም፣ ሰብሳቢ አጋሮቹም ECAs ላይ እጃቸው እንዲያስገቡ አይፈቅድም።**

6. *የገንዘብ ድጋፍ:* የገንዘብ ድጋፍ ማለት በገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው ላይ የተቀመጠው የገንዘብ እና ሌላ የብቁነት መስፈርት የሚያሟሉ ታካሚዎች በ MHHS ሆስፒታሎች አማካኝነት ለሚሰጡ ህክማናዊ ወሳኝነት ላላቸው እና አስቸኳይ ሕክምና ለሚጠይቁ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች መክፈያ ይሆናቸው ዘንድ በ MHHS የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ ነው። ድጋፍ ለማግኘት ብቁ የሆኑ ታካሚዎች መድህን የሌላቸው ታካሚዎች፣ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ታካሚዎች፣ እንዲሁም በከፊል የመድህን ሽፋን ያላቸው ሆነው ከቀሪ የሕክምና ክፍያዎቻቸው የተወሰነውን ወይም ሙሉውን መክፈል የማይችሉ ታካሚዎችን ያጠቃልላል። የገንዘብ ድጋፍ ከመድህን ኩባንያዎች እና ሌሎች ሶስተኛ አካል የጤና ሽፋን ጋር የተደረጉ ኮንትራቶች ላይ የተመሰረቱ ጥቅማጥሞችን አያካትትም።

7. *በቀላል ቋንቋ የተዘጋጀ ጥቅል መረጃ (“PLS”):* የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ የቀላል ቋንቋ ጥቅል መግለጫ የሚከተሉትን ያጠቃልላል: (a) የብቁነት መስፈርቶች እና የሚሰጠው ድጋፍ አጭር መግለጫ፤ (b) የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻዎች መውሰድ የሚቻልባቸው የድረገጽ እና አካላዊ መገኛዎች ዝርዝር፤ (c) ነጻ የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው ቅጂ እንዴት መውሰድ እንደሚቻል የሚያሳዩ መመሪያዎች፤ (5) የማመልከቻ ሂደቱ ላይ ድጋፍ የሚጠይቁበት አድራሻ የያዘ መረጃ፤ (6) የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው በሌላ ቋንቋ ተተርጉሞ የሚያገኙበት እና ሌሎች ተዛማጅ ሰነዶች፤ እንዲሁም (7) የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ የሆኑ ታካሚዎች በአጠቃላይ ለአስቸኳይ ሕክምና ወይም ህክምናዊ ወሳኝነት ላለቸው ሕክምናዎች ከሚጠየቁት የክፍያ መጠን የበለጠ ክፍያ እንደማይጠየቁ የሚያረጋግጥ መግለጫ።

8. *በቂ ጥረቶች:* MHHS ታካሚው ከሆስፒታል ከመውጣቱ በፊት የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲውን የሚመለከት የቀላል ቋንቋ ጥቅል መረጃ ለታካሚው በመስጠት ለታካሚው የ MHHS የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ በሚመለከት ማሳወቂያ ለመስጠት በቂ ጥረት ያደርጋል። በተጨማሪም፣ MHHS ታካሚዎችን ስለ MHHS የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ ለማሳወቅ የሚከተሉትን እርምጃዎች ይወስዳል:

    a. *ያልተሟሉ ማመልከቻዎች:* ታካሚው እና/ወይም ቤተሰቡ ያልተሟላ ማመልከቻ ቢያስረክቡ፣ ምን ተጨማሪ መረጃ ወይም ሰነድ እንደሚያስፈልግ የሚገልጽ የጽሑፍ ማሳወቂያ MHHS ይልክላቸዋል።

    b. *የተሟሉ ማመልከቻዎች:* ታካሚው እና/ወይም የታካሚው ቤተሰብ አባል የተሟላ የገንዘብ ድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻ ካስገቡ ደግሞ፣ MHHS በተገቢው ጊዜ ውስጥ ታካሚው ብቁ የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ መሆኑ ወይም አለመሆኑ የሚገልጽ የጽሑፍ ማሳወቂያ በተገቢው ጊዜ ይሰጣል እንዲሁም ይህ ውሳኔ የተወሰነባቸው ምክንያቶች ለታካሚው (የሚቻል ከሆነ፣ ታካሚው ብቁ የሆነበት ድጋፍ በመግለጽ ጭምር) በጽሑፍ ያሳውቃል። ይህ ማሳወቂያ፣ የተፈቀደው የገንዘብ ድጋፍ መቶኛ መጠን (ተቀባይነት ላገኙ ማመልከቻዎች) ወይም ጥያቄያቸው ውድቅ የተደረገባቸው ምክንያት(ቶች)፣ የሚያስኬድ ከሆነ ደግሞ ከታካሚው እና/ወይም ከቤተሰቡ የሚጠበቀው ክፍያ የሚያጠቃልል ይሆናል። ታካሚው እና/ወይም ቤተሰቦቹ ሞልተው ያስረከቡት ማመልከቻ በሚገመገምበት ጊዜ መግለጫዎች ይላኩላቸዋል።

    c. *የታካሚ መግለጫዎች:* MHHS የታካሚው ሂሳብ እና የሚከፈለው መጠን የሚገልጹ ተከታታይ መግለጫዎችን ይልካል። የታካሚው መግለጫዎች ታካሚው የመድህን ሽፋን ካለው ለ MHHS ማሳወቅ እንዳለበት የሚያሳስብ ጥያቄ፣ የ MHHS ገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ ማሳወቂያ፣ የገንዘብ ድጋፍ ለመጠየቅ የሚጠቀሙበት የስልክ ቁጥር፣ እንዲሁም የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው ሰነዶች የሚገኙበት ድረገጽ የሚያካትቱ ናቸው።

    d. *የ MHHS ድረገጽ:* የ MHHS ድረገጾች የገንዘብ ድጋፍ መኖሩን የሚገልጽ ማሳወቂያ ከገንዘብ ድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻው አሰራር ማብራሪያ ጋር በማድረግ ብዙ ሰው በሚያውቀው ቦታ ይለጥፋሉ። MHHS ይህንን የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ ሽፋን ካላቸው እና ሽፋን ከሌላቸው አቅራቢዎች ዝርዝር ጋር ከቀላል ቋንቋ የጥቅል መረጃ፣ የገንዘብ ድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻ፣ እንዲሁም የክፍያ አጠያየቅ እና አሰባሰብ ፖሊሲ የ MHHS ድረገጽ ላይ ይለጥፋል: http://www.memorialhermann.org/financialassistanceprogram/. MHHS የእነዚህ ሰነዶች ነጻ ቅጂዎች በጥያቄዎ መሰረት እንዲያገኙ በአስቸኳይ ሕክምና ዲፓርትመንት እና በመመዝገቢያ ቦታዎች ያዘጋጅላቹዋል።

**<u>የግምገማ መስፈርት:</u>**

1. *ተግባቦት ከታካሚ ጋር:* ገና የገቢ ኡደት ሂደት በሚከናወንበት ጊዜ፣ ታካሚዎች ገና መክፈል ስለሚገባቸው የሒሳብ መጠን፣ እንዲሁም ከ MHHS የሚጠበቁ ክፍያዎች በተመለከተ በጽሑፍ ወይም በቃል ሊነገራቸው ይገባል። ሁሉም ከታካሚው ጋር የሚደረጉ ተግባቦቶች የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ መኖር የሚገልጽ ማሳወቂያ፣ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት

የሚደውሉበት ስልክ ቁጥር፣ እንዲሁም የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው ቅጂዎች እና ተዛማጅ ሰነዶች የሚያገኙበት ድረገጽ አድራሻ የሚያካትቱ ይሆናሉ። MHHS የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው በተመለከተ በቀላል ቋንቋ የተዘጋጀ ጥቅል መረጃ ቅጂ ለሁሉም ታካሚዎች ይሰጣል።

a. መድህን የሌላቸው ታካሚዎች MHHS የእነሱን የጤና እንክብካቤ ወጪዎች ለመሸፈን የሚያስችሉ የገንዘብ ምንጮችን ከፌደራል እና ግዛት ፕሮግራሞች ለማግኘት ለማፈላለግ በሚያደርጋቸው ጥረቶች መተባበር ይጠበቅባቸዋል። መድህን የሌላቸው ሰዎች የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው እና አገልግሎቱ ካገኙበት ቀን በኋላ እስከ 150 ቀናቶች ድረስ የሚኖራቸው ያልተከፈለ ሒሳብ የሚገልጽ ወርሀዊ መግለጫ ይደርሳቸዋል። ታካሚዎች ወደ ክፍያ እቅድ መግባት ካልቻሉ ወይም ላልተከፈለ ሂሳባቸው እልባት የማይሰጡ ከሆነ ፣ MHHS ሒሳቡን ወደ ሶስተኛ አካል ሰብሳቢ ኤጀንሲ መመደብን እንደ መፍትሄ ሊወስደው ይችላል።

b. መድህን ያላቸው ታካሚዎች MHHS ከታካሚው መድህን ድርጅት ክፍያዎችን ለመቀበል በሚያደርገው ጥረት ትብብር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በተጨማሪም MHHS የታካሚው መድህን ሽፋን ሰጪ ድርጅትን ቢያስከፍለውም ይህ መልካም እርዳታ እንጂ የታካሚውን ከ MHHS ላገኛቸው አገልግሎቶች የመክፈል ሃላፊነት ያስቀራል ማለት እንዳልሆነ ታካሚው መረዳት ይኖርታል። ስለዚህ፣ አንዳንድ ጊዜ ታካሚው ተደጋጋሚ የክፍያ መዘግየትን ለመፍታት ወይም ሌሎች ለአገልግሎት መከፈል ያለበት ክፍያ እንዳይከፈል የሚከለክሉ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን ለመፍታት ከመድህን ሰጪ ድርጅቱ ጋር ተቀራርቦ እንዲሰራ MHHS ሊያስገድደው ይችላል። MHHS ለሰጣቸው አገልግሎቶች ክፍያዎችን ከተቀበለ በኋላ እና ሒሳቡ ላይ ተገቢ የኮንትራት መስተካከያዎች ከተደረጉ በኋላ ታካሚው የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲውን እንዲሁመ የመድህን ሰጪ ድርጅቱ ክፍያ የፈጸመባቸው ቀናቶች አንስቶ እስከ 120 ቀናቶች ድረስ የሚኖራቸው ያልተከፈለ ሒሳብ የሚገልጽ ወርሀዊ መግለጫ ይቀበላል። ታካሚዎች ወደ ክፍያ እቅድ መግባት ካልቻሉ ወይም ላልተከፈለ ሂሳባቸው እልባት የማይሰጡ ከሆነ፣ MHHS ሒሳቡን ወደ ሶስተኛ አካል ሰብሳቢ ኤጀንሲ መመደብን እንደ መፍትሄ ሊወስደው ይችላል።

2. *የገንዘብ ድጋፍ:* ታካሚዎች ያወጡት ወጪ ከሶስተኛ አካላት ምንጮች እንዲመለስላቸው መተባበር የተለመደ የ MHHS ተግባር ነው። ታካሚዎች የሚሆናቸው የፌዴራል ወይም የግዛት የጤና እንክብካቤ ሽፋን ፕሮግራሞች በመፈለግ ረገድ፣ እንዲሁም የገንዘብ ድጋፍ ብቁነታቸው በመወሰን ረገድ የገንዘብ ምክር አገልግሎት ድጋፍ አይለያቸውም። ክፍያ የመሰብሰብ እንቅስቃሴ እነዚህ ውሳኔዎች እስኪታወቁ ድረስ በይደር ይቆያሉ፣ የታካሚ መግለጫዎች ግን መላካቸውን ይቀጥላሉ። በ MHHS አማካኝነት የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ በተመለከተ፣ የቅናሹ መጠን ለማስላት ጥቅም ላይ የሚውለው መስፈርት፣ MHHS የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲውን በ MHHS ለሚገለገለው ማህበረሰብ በሰፊው ለማስተዋወቅ የሚወስዳቸው እርምጃዎች፣ MHHS የገንዘብ ድጋፍ ብቁነት ውሳኔ ለመወሰን የሚጠቀምበት አሰራር፣ እና የማመልከቻ ሂደቱ በ **MHHS የገንዘብ ድጋፍ** ፖሊሲው ላይ በዝርዝር ተገልጸዋል።

3. *የክፍያ እቅዶች:* MHHS ክፍያዎቻቸው ለመክፈል ሊቸገሩ እንደሚችሉ ለሚገምቱ ታካሚዎች ከወለድ-ነጻ፣ የተራዘሙ የአከፋል እቅዶችን ይሰጣል። ታካሚዎች የክፍያ እቅዳቸውን በ My Bill Patient Portal አማካኝነት ማስገባት ይችላሉ (https://paymybill.memorialhermann.org/?_ga=1.221977755.265979238.1484666437)። ታካሚዎች ንቁ የክፍያ እቅድ ለማስቀጠል ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ክፍያ መፈጸም ይጠበቅባቸዋል። ታካሚው በታቀደው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የማይከፍል ከሆነ ያልተከፈለ ክፍያው ለመክፈል ቃሉን ወደ ተግባር የማይቀይር አታላይ ተደርጎ ይቆጠራል። የመጀመሪያ የተዛባ ወይም በተገቢው ጊዜ ያልተከፈለ ክፍያ ተከትሎ የታካሚውን የክፍያ እቅድ እንደገና ለመመስረት በቂ ጥረት ይደረጋል። ታካሚው የክፍያ እቅድን እንደገና ሊመሰርት ካልቻለ እና/ወይም ለሁለተኛ ጊዜ ቃሉን ጠብቆ መክፈል ሳይችል ከቀረ MHHS ሒሳቡን ወደ ሶስተኛ አካል ሰብሳቢ ኤጀንሲ ያዞረዋል። የታካሚው ሂሳብ ወደ ሶስተኛ አካል ሰብሳቢ ኤጀንሲ ከተዘዋወረ በኋላ ታካሚው ያልተከፈሉ ሒሳቦቹ ለመክፈል በቀጥታ ከሶስተኛ አካል ኤጀንሲው ጋር መስራት ይጠበቅበታል።

ታካሚው ለተጠቀሰው ሒሳብ በ MHHS Everyday Well Patient Portal አማካኝነት ወደ ሌላ የክፍያ እቅድ ብቁ መሆን አይችልም። ይሁን እንጂ፣ ታካሚው ቀጥለው ለሚመጡ ሒሳቦች በ Everyday Well Patient Portal አማካኝነት የክፍያ እቅድ ለመመስረት ብቁ መሆን ይችላል።

4. *ክፍያ በማይፈጸምበት ከንውን ላይ ክፍያ መሰብሰብ:* ክፍያ የማይፈጸምበት ከንውን በሚከናወንበት ጊዜ፣ ብዙ በሒሳብ መጠን ላይ፣ የሶስተኛ አካል ከፋይ ወጪ የማካካስ ሀላፊን፣ የታካሚው የመንግስት ገንዘብ ወይም የገንዘብ ድጋፍ የማግኘት ብቁነት፣ የታካሚው ትብብር፣ የክፍያ ወይም እዳ መክፈል ያለመቻል ታሪክ፣ እና/ወይም ታካሚውን ማግኘት ያለመቻል ሁኔታ ላይ የተመሰረቱ የተለያዩ የአሰባሰብ እንቅስቃሴዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ። የክፍያ መሰብሰብ እንቅስቃሴዎቹ የከፋይ ሶስተኛ አካል እምቢታ ይግባኝ፤ ከከፋይ ሶስተኛ አካሉ ጋር የሚደረግ ተግባቦት መከታተል፤ ለታካሚው የገንዘብ ድጋፍ ለማቅረብ እና/ወይም ክፍያ ለመጠየቅ የሚያስችሉ መግለጫዎች፣ ደብዳቤዎች፣ እና በተሌፎን ስልክ መደወል፤ እንዲሁም ሒሳቡ በገባው ቃል መሰረት እየከፈለ እንዳልሆነ እና ታካሚው ያልከፈለው የሒሳብ መጠን የሚገልጽ የመጀመሪያ ማሳወቂያ ከተላከለት ቀን አንስቶ ከ 120 ቀናቶች በኋላ ሒሳቡ ለሶስተኛ አካል ሰብሳቢ ድርጅት ተላልፎ ሊሰጥ እንደሚችል የሚገልጽ የመጨረሻ ማሳወቂያ ለተካሚው ወይም ለተያገዥ መላክን ሊያጠቃልል ይችላል። MHHS ለሒሳቡ በተገቢው ጊዜ ያለመከፈል ሀላፊነት የሚወስደው ሶስተኛ አካል (የሶስተኛ አካል ተጠያቂነት) ላይ ክስ ሊመሰርትም ይችላል።

5. *ሊመለስ የማይችል ወይም የባከነ እዳ:* ሒሳቦች የባከኑ ተብልው ሊወሰዱ የሚችሉት ሂሳቡ ለመጨረሻ ጊዜ ለከፋይ ሶስተኛ ኣካል(ሎች) እና ለታካሚው/ተያገዡ ከተከፈለ፣ የክፍያ መጠየቂያ ከተመሰረተ እና የክትትል ተግባቦቶች ከተካሄዱ፣ ለታካሚው የገንዘብ ድጋፍ መኖሩን ለማሳወቅ በቂ ጥረቶች ከተደረጉ፣ የክፍያ የጊዜ ገደቦች ካለፉ፣ እንዲሁም ሒሳቡ ሊሰበሰብ የማይችል መሆኑ ውሳኔ ላይ ከተደረሰ በኋላ ነው።

6. *ውጫዊ የአሰባሰብ እርምጃዎች:* ተገቢ ሒሳቦች ብቻ የባከኑ እዳዎች ወይም የማይመለሱ ተብለው መፈረጃቸውን ለማረጋገጥ፣ ሒሳቡ ለውጫዊ ሰብሳቢ አካል መዘዋወርን ጨምሮ በቂ የክፍያ መጠየቅ እና መሰብሰብ ጥረቶች ከተደረጉ በኋላ ብቻ ነው የገቢዎች አገልግሎት ቡድኑ ሊሰበሰብ አይችልም የተባለውን ሒሳብ የባከነ ተብሎ እንዲያዝ ለማጽደቅ ወደ መገምገም የሚሄደው። ሁሉም የአሰባሰብ መስፈርቶች ተጠቅሞ በቂ ጥረት ከተደረገ እና ሒሳቡ ሊከፈል የማይችል ተብሎ ከጸደገ በኋላ፣ ደንበኛው ላይ ገደብ ይጣላል  ወይም ለገቢዎች ኡደት አስተዳደር ምክትል ፕረዚደንት ተገቢውን እርምጃ መጠቆም። በተጨማሪም ሒሳቦች በተመሰረተው ከፋይ፣ የሒሳብ መጠን፣ እና የክፍያ እንቅስቃሴ መለኪያዎች መሰረት በታካሚው የሒሳብ ስርአት በቀጥታ ለውጫዊ ክፍያ ሰብሳቢ አካል ተላልፎ ሊሰጥ ይችላል።

7. *አፈጻጸም:* ይህንን ፖሊሲ የማስፈጸም እና ለዲፓርትመንቶች የሚሆኑ የአስተዳደር አሰራሮችን የማዘጋጀት ስልጣን ለ MHHS ገቢዎች ኡደት አስተዳደር ክፍል የተሰጠ ነው።

**<u>ማጣቀሻዎች:</u>**

A. የታካሚ ዝውውር ፖሊሲ (EMTALA እና የቴክሳስ ዝውውር ድንጋጌ ማክበር)
B. የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ
C. የገንዘብ ድጋፍ በተመለከተ በቀላል ቋንቋ የተዘጋጀ ጥቅል መረጃ
D. የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ